የሰ/መ/ቁ. 83701

ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ ህንደያ እንድሪስ ወኪል አብዲ ዓሊ - ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የወጪና ኪሳራ አወሳሰን ሥርዓትን አስመልክቶ በተነሳ ክርክር ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በቀዳሚነት የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ጉዳይ በየትኛው ዓይነት መዝገብ ቀርቦ ሊታይ ይገባል? የሚለውን አስመልክቶ ያቀረበውን ክርክር አግባብነት ተመልክተናል፡፡

አመልካች ይህ ብር 10,000.00 እንድንከፍል የተወሰነብን የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው በአፈፃፀም መዝገብ ሆኖ ሳለ በተዘጋውና ዋናው ጉዳይ የታየበት መዝገብ ተንቀሳቅሶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ የአፈፃፀም መዝገቡ ደግሞ በበላይ ፍ/ቤት ታግዷል፡፡ ስለሆነም ይህ የወጭና ኪሳራ ጉዳይ የሚታይበት ሥርዓት ሳይኖር የተወሰነብን አወሳሰን ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁን እንጂ በአፈፃፀም ጉዳይ ቀርቦ ሊታይ የሚገባው ማናቸውም ጉዳይ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 ተደንግጓል፡፡

ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነው ፍርድ ከሚያካትታቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ፍርዱን ለማስወሰን ሲባል በክርክር ምክንያት የወጣው የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 183 በግልፅ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም ወጭና ኪሳራን ግን እንደሚከፍል በዋናው ጉዳይ ተለይቶ ከተወሰነ በኋላ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463 መሰረት የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ዋናው ፍርድ ባረፈበት መዝገብ ላይ ቀርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ስለቀረበው የወጭና ኪሣራ

አስፈላጊነት፣ ስለመጠኑ እና በእርግጥም ወጭና ኪሳራ ስለመውጣቱ የበኩሉን ክርክር ካቀረበ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 464 እንደተመለከተው የወጭና ኪሳራ ልኩ ይወሰናል፡፡

እንግዲህ የወጭና ኪሳራ አወሳሰን ሥርዓት ይህ ከላይ የተመለከተው በመሆኑ የአሁን አመልካች የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው በአፈፃፀም መዝገብ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው፣ የፍርድ አፈፃፀምን ጉዳይ መነሻ ሀሳብ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤቱ በወጭና ኪሳራ መልክ የቀረበውን እና ለጠበቃ ተከፈለ የተባለውን የጥብቅና አበል በሚመለከት በማስረጃነት የቀረበው የጥብቅና ውል ከጊዜ ቅደም ተከተል አንፃርም ሆነ ከጠበቃው ማንነት አንፃር በአስረጅነቱ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ከገለፁ በኋላ በሌላ በኩል ጠበቃ ተስፋሁን የተባለ ሌላ ጠበቃ በዋናው ጉዳይ ጊዜ የነበረ መሆኑን መታመኑን እና የጥብቅና አበል መጠን ክርክር በተደረገበት የገንዘብ መጠን አስራት መነሻ ተደርጎ የቀረበውን ባለመከተል ጉዳዩን ለመከታተል ወጣ ሊባል የሚችለው የጥብቅና አበል መጠን ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ነው ሲል ስለመጠኑም የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 በፍ/ቤቱ የተሰጠውን ፍቅድ ሥልጣን ከጉዳዩ ጋር በማዛመድ ተመልክቶ የወሰነው በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ ባለመግኘታችን ምክንያት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የሐረሪ ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 02260 መስከረም 09 ቀን 2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የጥብቅና አበልን አስመልክቶ የሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት ፀንቷል፡፡
2. ቀደም ሲል በመ/ቁ 07208 የተጀመረው የአፈፃፀም ክስ ታግዶ እንዲቆይ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ የሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ